| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ድርሰት ። |
| ርእስ ፤ | "መልክት ፡ ለማወራኛዎች ። " |
| ደሁሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ነሐሴ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፡ ቊ.2011-003 |
| ማስታወሻ ፤ | "ክዋኔ" ፡ ዐምድ ። |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ክዋኔ

CONSTITUTION | دستور

*[በዚህ ፡ ዐምድ ፥ ስለሕገ ፡ መንግሥት ፡ (ወይም ፡ ክዋኔ) ፡ ጉዳይ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሐሳቦችና ፡ አስተያየቶች ፡ ይቀርቡበታል ። ]*



# መልክት ፡ ለማወራኛዎች ።

ያንድ ፡ ሀገር ፡ ሕዝብ ፥ ርስ ፡ በርሱ ፡ የሚነጋገርበት ፡ አንድ ፡ **ሀገራዊ ፡ ቋንቋ ፡ ወይም ፡ ልሳን** ፡ አለው ፤ ሀገራዊ ፡ ቋንቋው ፡ ቢነካበት ፥ ሀገራዊ ፡ ህልውናው ፡ እንደተነካበት ፡ ይቈጠራል ።

ዛሬ ፡ ታሪካዊ ፡ ወቅት ፡ ላይ ፡ ደርሰናል ። የወደ ፡ ፊት ፡ ዕጣ ፡ ፈንታችን ፡ ወይ ፡ እሚሰምርበት ፥ አለዚያም ፡ ምናልባት ፡ ለዘለቄታው ፡ እሚበላሽበት ፡ ረድፍ ፡ ላይ ፡ እንገኛለንና ፤ እያንዳንዳችን ፡ ኀላፊነት ፡ አለብን ። በተለይ ፡ ደግሞ ፥ ማወራኛዎች ፡ (media) ፥ በሚለፍፉት ፡ ዜናና ፡ በሚነዙት ፡ አስተያየት ፡ የሚያለሙትን ፡ ያኽል ፡ ሊያጠፉም ፡ ይችላሉና ፥ ታላቅ ፡ ኀላፊነት ፡ አለባቸው ።

የማወራኛዎች ፡ ዋጋ ፡ በሚዘግቡት ፡ ወሬ ፥ በቃሉ ፡ ትኽክልነት ፥ በይዘቱ ፡ እውነተኛነት ፡ ይለካል ።

## 1 ፤ የቃል ፡ ትኽክልነት ።

የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ በመካድ ፥ "የኢትዮጵያ ፡ ሕዝቦች" ፡ እያሉ ፡ ትኽክለኛ ፡ ወሬን ፡ መዝገብ ፡ ይቻላልን ፧ ወይስ ፡ አለትርጉሙ ፥ "ብሔር ፣ ብሔረሰቦች" ፡ እያሉ ፧ ወይም ፡ ደግሞ ፡ አላግባብ ፡ "ክልል" ፡ እያሉ ፧

ቃላቱ ፡ አሉ ፥ የዋሉበት ፡ ጉዳይ ፡ ግን ፡ አይገለጥባቸውም ። አወራኚው ፡ ለጉዳዩ ፡ ትኽክለኛውን ፡ ቃል ፡ አግኝቶ ፡ ማዋል ፡ ይጠበቅበታል ። ካ 40 ፡ ዓመታት ፡ ወዲህ ፡ በተለይ ፡ የግዛት ፡ ግሳችን ፡ መዘበራረቅ ፡ አግኝቶታል ። የተዘበራረቀውን ፡ ለማስተካከል ፡ ከመዝገበ ፡ ቃላት ፡ የተሻለ ፡ መሣሪያ ፡ አይገኝም ።

በማናውቀው ፡ ቋንቋ ፡ ከመጻፋችን ፡ በፊት ፡ ቋንቋውን ፡ እንማራለን ፤ ከተማርነውም ፡ ወዲያ ፥ ስንጽፍበት ፥ መዝገበ ፡ ቃላትን ፡ ይዘን ፡ እያጣራን ፡ እንጂ ፥ "በይመስለኛል" ፡ አንጽፍም ። ዐማርኛ ፡ ሀገራዊ ፡ ቋንቋችን ፡ ነው ፤ አድገንበታል ፣ ተምረነዋልም ። ኾኖም ፥ በሀገራዊ ፡ ቋንቋችን ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ የትርጒም ፡ መፋለስና ፡ መዘበራረቅ ፡ ተገንዝበን ፥ ተፈላጊውን ፡ ጥንቃቄ ፡ እያደረግን ፡ ልንጽፍ ፡ ልንናገር ፡ ይገባል ።

ሀገራዊ ፡ መግባቢያችን ፡ ዐማርኛ ፥ ይህን ፡ ዕንቅፋት ፡ በተፈጥሮው ፡ የተሻገረው ፡ ቢኾንም ፥ በገቢር ፡ ገና ፡ ያልተሻገርነው ፡ አለንና ፥ ፈጥነን ፡ ልንሻገረው ፡ ይገባል ። ለዚህም ፡ ሌላ ፡ ዘዴ ፡ የለም ፤ በመዝገበ ፡ ቃላት ፡ እያጠራን ፡ ለመጻፍና ፡ ለመናገር ፡ እንትጋ ። "ልግም ፥ እግዜር ፡ አይወድም" ፡ ነውና ፥ ስንፍናንና ፡ ልግምን ፡ እናስወግድ ።

ከዚሁ ፡ ጋራ ፥ ማወራኛዎች ፡ የመጥፎ ፡ አርኣያ ፡ ማዛመቻ ፡ ሊኾኑ ፡ አይገባቸውም ። ለምሳሌ ፡ አንዳንድ ፡ ባለጊዜዎች ፡ ቀርበው ፡ በሚናገሩበት ፡ ጊዜ ፥ በራስ ፡ ካለመተማመን ፡ የተነሣ ፥ "ተምረዋል" ፡ የሚያሠኛቸው ፡ እየመሰላቸው ፥ የማያስፈልጉ ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቃላትን ፡ ካማርኛው ፡ እየዘነቁ ፡ መናገርን ፡ ይዘዋል ። ዕርማቱ ፡ ለሚያሻቸው ፡ ተናጋሪዎች ፥ ከንግግሩ ፡ በፊት ፥ ገለል ፡ አድርጋችኹ ፥ ነውር ፡ መኾኑን ፡ እያሳሰባችኹ ፡ ብትቃኟቸው ፡ ጥሩ ፡ ነው ።

## 2 ፤ የወሬ ፡ ታማኝነት ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

የማወራኛ ፡ ሥራ ፡ ትልቅ ፡ ዐቅምን ፡ የሚጠይቅ ፡ የድርጅት ፡ ሥራ ፡ ነውና ፥ ዐቅሙ ፡ የሌለው ፡ በድጐማ ፡ ሊሠራ ፡ ይገደዳል ።

***"የመንግሥት" ፡ ማወራኛዎች*** ፥ የማያጥጥ ፡ የገንዘብ ፡ ምንጭ ፡ ያለላቸውን ፡ ያኽል ፥ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ በሌለበት ፡ ኹኔታ ፡ የታማኝነት ፡ ችግር ፡ አለባቸው ።

*"የሚከፍል ፡ ያዛል"* ፤ በድጐማ ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ **የግል ፡ ማወራኛ** ፡ ድርጅት ፡ ነጻ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አያስደፍርም ። በቅርቡ ፡ አንዳንድ ፡ ማስረጃዎችን ፡ አይተናል ።

ዛሬ ፡ ደግሞ ፥ በኢንተርኔት ፡ ዘመን ፥ **ማኅበራዊ ፡ ማወራኛ** ፡ (social media) ፡ የውርኝቱ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኾኗል ። ወጪው ፡ አነስተኛ ፡ ነው ፤ የሚያ ፡ ብቃትን ፣ የድርጅት ፡ ምላትን ፣ የአቋም ፡ ግዑዝነትን ፡ (neutrality) ፡ ስለማሟላቱ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ዋስትና ፡ የለም ።

በእነዚህ ፡ ሦስት ፡ ክፍሎች ፡ የሚመደበውን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የማወራኛ ፡ ዐቅም ፥ ከተያዘው ፡ ሀገርን ፡ የመታደግ ፡ ትግል ፡ ለማሳተፍ ፥ ከእያንዳንዱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ማወራኛ ፡ መዠመር ፡ ይኖርብናል ።

ከ*"መንግሥት"* ፡ ማወራኛው ፡ ብንዠምር ፥ ባለፉት ፡ 28 ፡ ዓመታት ፡ እንዳየነው ፥ ከዋና ፡ አዘጋጅ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ተላላኪው ፥ ባብዛኛው ፡ የሕ.ወ.ሐ.ት. ፡ አባላት ፡ በመኾናቸው ፥ አሳምኖ ፡ ማሳተፉ ፡ ከንቱ ፡ ይመስላል ። ካንድ ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ ደግሞ ፥ ቅጥሩ ፡ ወደ ፡ *"ብዝኀነት"* ፡ ያመራል ፡ ተብሎ ፡ ሲጠበቅ ፥ በተወሰኑ ፡ የሕ.ወ.ሐ.ት. ፡ አባላት ፡ ምትክ ፡ የዐቅዳዊ ፡ ሸሪኩ ፡ የኦ.ዴ.ፓ. ፡ አባላት ፡ ተተክተዋል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ከያግጣጫው ፡ ይሰማል ፤ ሌላ ፡ የሚያጓጓ ፡ ነገር ፡ የለውም ። ባኹኑ ፡ ኹኔታ ፥ በ*"መንግሥት"* ፡ ማወራኛ ፡ በኩል ፥ በነጻነት ፡ ሊሠራ ፡ የሚችል ፡ አወራኚ ፡ አይጠበቅም ።

በግል ፡ ማወራኛ ፡ ድርጅቶች ፡ በኩል ፡ ይልቅ ፡ የተስፋ ፡ ጭላንጭል ፡ አለ ። በ*"መንግሥት"* ፡ ማወራኛ ፡ አንጻር ፥ እላይ ፡ የጠቄምነው ፡ ድጐማ ፡ ካልገታው ፡ በቀር ፥ የግሉ ፡ ማወራኛ ፡ የተሻለ ፡ ነጻነት ፡ አለውና ፥ ገበያውን ፡ (አንባቢውን ፣ አድማጩንና ፡ ተመልካቹን) ፡ ለመቈጣጠር ፡ አይቸግረውም ። የገበያው ፡ ዐቅም ፡ ከደጓሚ ፡ ነጻ ፡ ያወጣዋል ፡ የሚል ፡ ተስፋ ፡ አለ ።

በተመሳሳይ ፥ የማኅበራዊ ፡ ማወራኛ ፡ አባላት ፥ በየግላቸው ፡ ነጻ ፡ የመኾን ፡ ወይ ፡ ያለመኾን ፥ ባለሚያ ፡ የመኾን ፡ ወይ ፡ ያለመኾን ፡ ችግር ፡ ቢገድባቸው ፡ እንጂ ፥ እውነተኛና ፡ ታማኝ ፡ ወሬን ፡ በተስተካከለ ፡ አገላለጽ ፡ ከመልፈፍ ፡ የሚከለክላቸው ፡ የለም ። ካኹኑ ፡ ያቈጠቈጡት ፡ እሳት ፡ የላሱ ፡ ዜነኛዎች ፡ ይህን ፡ ተስፋ ፡ አለምልመውታል ።

እስካኹን ፡ የተነገረው ፡ እንደተያዘ ፡ ኾኖ ፥ ለኹሉም ፡ የማወራኛ ፡ ክፍሎች ፡ የሚከተለውን ፡ መልክት ፡ በትሕትና ፡ እናስተላልፋለን ። መልክቱ ፡ ዐዲስ ፡ አይደለም ፤ በማወራኛ ፡ ሚያ ፡ የሠለጠነ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ያውቀዋል ። ነገር ፡ ግን ፥ በዘመናችን ፡ በብዙ ፡ ረገድ ፡ በገቢር ፡ ስላልተከበረ ፥ ማስታወሱ ፡ ይጠቅማል ፦

ሀ) ***"ከሺሕ ፡ ወርዋሪ ፥ አንድ ፡ መዐት ፡ አውሪ"*** ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በዚህች ፡ ሰዓት ፡ በሀገሩ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ እግዚእናውን ፡ ለማስከበር ፡ በያግጣጫው ፡ ተነሣሥቷል ። በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ ዐዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ለመሥራትና ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥቱን ፡ ለመመሥረት ፡ ይቻለው ፡ ዘንድ ፥ የማወራኛ ፡ ድርጅቶች ፥ በለፈፋዎቻቸው ፥ ቃላትን ፡ መርጠው ፣ ዜናን ፡ አጣርተው ፡ ያቅርቡለት ። ቢደፍሩ ፡ ደግሞ ፥ የትግሉን ፡ ዜና ፡ ይዘግቡለት ፤ አንደበትም ፡ ይኹኑት ። እስካኹን ፡ ይህኑ ፡ ሲፈጽሙ ፡ የቈዩትን ፡ እናመሰግናለን ።

በ) ***"ሳያስረግጡ ፡ ወሬ ፤ ሳይገድሉ ፡ ጐፈሬ"*** ፤ ከውጭም ፡ ከውስጥም ፡ የሚተላለፉላቸውን ፡ በተለይ ፡ የአኃዝ ፡ መረጃዎች ፡ በሚገባ ፡ ሳይፈትሹ ፡ እንዳለ ፡ በማወራኘት ፡ የአጥፊ ፡ *"ፕሮፐጋንዳ"* ፡ መሣሪያ ፡ አይኹኑ ። ቢችሉ ፥ ራሳቸው ፡ የመረጃው ፡ ምንጮች ፡ ይኹኑ ፤ እቦታው ፡ ድረስ ፡ እየኼዱ ፡ መረጃውን ፡ አጠናቅረው ፡ ለሕዝብ ፡ ያቅርቡት ። ካሉባልታ ፡ ይልቅ ፡ ርግጠኛውን ፡ ወሬ ፣ ውለኛውን ፡ መረጃ ፡ ያወራኙ ።

ገ) ***"እውነቱን ፡ ተናግሮ ፡ እመሸበት ፡ ያድሯል"*** ፤


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ሰብኣዊ ፡ መብት ፡ ሲጣስ ፥ የሀገር ፡ ደኅንነት ፡ ላደጋ ፡ ሲጋለጥ ፥ ውሸት ፡ ሲሰበክ ፥ ሙስና ፡ ሲፈጸም ፥ ወዘተ. ፥ አይተው ፡ እንዳላዩ ፣ ሰምተው ፡ እንዳልሰሙ ፡ አይኾኑ ። ደኅና ፡ ቀን ፡ እንዲወጣ ፡ እንደ ፡ እስክንድር ፡ ነጋ ፡ ይጋፈጡ ።

ሕዝብም ፥ የሚያምኑትን ፡ ሳይኾን ፥ ለእውነት ፡ ብለው ፡ ውድ ፡ ዋጋን ፡ የሚከፍሉለትን ፡ ወገኖቹ ፡ የኾኑትን ፡ ዜነኛዎች ፡ ከመደገፍና ፡ ከመጠበቅ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አይልም ። እስካኹን ፡ የቸገረው ፥ እውነተኛውን ፡ ከግብዙ ፡ (ወይም ፡ ከግዙው) ፡ መለየቱ ፡ ነበር ፤ ነገሩ ፡ እየጋመ ፡ ሲኼድ ፥ እውነተኛውና ፡ ሌላው ፡ እያደር ፡ ይለያል ።

አደጋ ፡ ውስጥ ፡ ኾነው ፥ እነዚህን ፡ የማወራኛ ፡ ግዴታዎች ፡ ሳያጓድሉና ፡ ሳያዛንፉ ፡ ጠንቅቀው ፥ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ኅብረተሰባቸውን ፡ በታማኝነትና ፡ በቅንነት ፡ ያገለገሉትን ፥ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ውድ ፡ የሕይወት ፣ የአካል ፣ የሀብት ፣ የንብረት ፡ ዋጋን ፡ የከፈሉልንን ፡ ክቡራት ፡ ኢትዮጵያውያትና ፡ ክቡራን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ዜነኛዎች ፡ ኹሉ ፥ እጅ ፡ እየነሣን ፥ ለገሮግና ፡ የሚገባውን ፡ ሰላምታ ፡ በሀገር ፡ ፍቅር ፡ እንሰጣቸዋለን ። ዋጋቸውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ አምላክ ፡ ይክፈልልን ፨


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።